# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም አገልግሎት ብቃት ማረጋገጥን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ/2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ............................................................................................i
ክፍል አንድ ......................................................................................4
መግቢያ...........................................................................................4
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አመሠራረት ..........................................................4
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ..............................................................5
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ........................................6
የሰው ኃይል .....................................................................................6
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ .............................................................7
የኦዲቱ ዓላማ .....................................................................................7
የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........................................................................7
ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ........................................7
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) .......................................................8
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria).................................8
የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description)..............................................8
ክፍል ሁለት ....................................................................................11
ግኝቶች.........................................................................................11
2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃ መስጠት፣ የፈቃድ አሰጣጥ እና ብቃት የማረጋገጥ ተግባርን ለመፈፀም የዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ..........................................................11
የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የሚመለከት ፖሊሲ አፈጻጸምን በተመለከተ ...11
የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃ አሰጣጥን በተመለከተ.........................12

ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) በተመለከተ ........ 15

የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት አካበቢዎች ጽዳትን በተመለከተ ........ 17

በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች ግንባታን በተመለከተ........ 17

በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡትን የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በተመለከተ ........ 20

በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች፣ሎጆች እና አስጎብኚ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት ንብረቶች መረጃ አያያዝና ልውውጥን በተመለከተ፣........ 21

የቱሪዝም አገልግሎትን ለማበረታታት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶች ለተባለላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን የሚደረገውን ክትትል በተመለከተ ........ 22

2.2 **የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመረጃ አያያዝ፤ አደረጃጀት እና አጠቃቀም ፈጣንና ጥራት ያለው ሥርዓት እንዲዘረጉ ማድረጉን እና ቱሪስቶቹን የሚመለከቱ መረጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የልውውጥ ሥርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ** ........ 23

የቱሪስት አገልግሎት የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፤ አደረጃጀት እና አጠቃቀምን በተመለከተ ........ 23

2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ........ 25

የቱሪስት አገልግሎት በሚሰጡ የዘርፍ ተቋማትና የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋርያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ ........ 25

የቱሪዝም አገልግሎት መስጪያ ተቋማት የፈጠሩትን የሥራ ዕድል በተመለከተ........ 26

በኮከብ ደረጃ ላሉ ሆቴሎች የሚሰጥ በውጪ ምንዛሪ የመገበያየት ፈቃድን በተመለከተ ........ 28

ክፍል ሦስት ........ 30

መደምደሚያ ........ 30

ክፍል አራት ..................................................................................... 32
የማሻሻያ ሃሳቦች ............................................................................... 32
አባሪ 1፡ ድርጅታዊ መዋቅር ............................................................................ 35
አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት .................................................................. 36

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቱሪዝም በዓለማችን ትኩረት ከተሰጣቸው በየጊዜው እድገትና ውጤት በማስገንዘብ ላይ የሚገኙ የልማት ዘርፎች አንደኛው ሲሆን ሴክተሩ ለታደጊም ሆነ ለበለፀጉ አገሮች ሰፊ የስራ እድል ከመፍጠሩ፣ የውጪ ምንዛሪን ገቢን ለማሳደጉ፣ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ የንግድና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በማስፋፋት በአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎችን ከማስገኘቱ ባሻገር በሕዝቦች መካከል መግባባት እንዲፈጠርና መልካም ግንኙነት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ የሚገኝ ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ ነው፡፡

2. የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባሕላዊ እሴቶችና ገፅታዎችን በእኩልነት ለመጠበቅና ለማሳደግ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ያለውን የቱሪዝም ዘርፍ በመደገፍና በማፋጠን ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች በሕብረተሰቡ እና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በማጥናት፣ በመጠበቅ ፣ በማልማት፣ በማስተዋወቅ እና የአገሪቷን መልካም ገፅታ በመገንባት ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም እንዲሰጡ በማድረግ እንዲሁም ለድህነት ቅነሳ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከሚያበረከቱ የኢኮኖሚ ሴክተሮች ውስጥ አንዱ ሆኖ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

## የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር አመሠራረት

3. አሁን የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል የሚታወቀው የአገሪቱ የቱሪዝም ስራ የሚስፋፋበትና አስፈላጊ የሆኑ ድርጅቶች የሚቋቋሙበትን እንዲያቅድና ዕቅዱንም ሥራ ላይ እንዲያውል መስከረም 11 ቀን 1957 በትዕዛዝ ቁጥር 36/1957 ዓ.ም "የኢትዮጵያ ቱሪስት ድርጅት" በሚል ስያሜ የተቋቋመ ነው:: ከአስር ዓመታት በኋላ ደግሞ ጳጉሜ 4 ቀን 1967 ዓ.ም በደንብ ቁጥር 21/1967 "የኢትዮጵያ ሆቴሎችና ቱሪዝም ድርጅት" በሚል በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር ተደራጅቶ የመንግስት ሆቴሎችና ሌሎችንም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በስሩ እንዲተዳደሩና እንዲቆጣጠራቸው ተደርጓል፡፡ቀጥሎም በደንቡ የተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነቱን እንደያዘ በአዋጅ ቁጥር 182/1972 እንደገና "የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን" በሚል ስያሜ ተዋቅሮ የተሰጡትን ስልጣንና ኃላፊነት ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከተመሰረተ በኋላ የመስሪያ ቤቱ ስም ሳይቀየር የቱሪዝም ኮሚሽን ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 11/1987 እንደገና ተቋቁሟል፡፡ ሆኖም ቀድሞ ኮሚሽኑ ያስተዳድራቸውና ይቆጣጠራቸው የነበሩ የመንግስት ሆቴሎችና ሌሎች የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው እንዲቋቋሚ እና እንዲሁም ፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓት መሰረት የክልል ቱሪዝም ቢሮዎች እራሳቸውን ችለው እንዲቋቋሙ በመደረጋቸው የኮሚሽኑ ዋና ዓላማ ቱሪዝም እንዲስፋፋና እንዲዳብር ማድረግ እንደሆነ በአዋጅ ተገልጿል፡፡

5. በመጨረሻም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን እንዲያስችል በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ተሰይሟል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

6. **የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት የተሰጡት ሥልጣንና ተግባር**

- የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ፣ ባህላዊ ቅርሶችና እሴቶች እንዲጠኑና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
- ኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎች እንዲጠኑና ሥነጽሑፎቻቸው እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማኅበራዊ እድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ተግባሮች ያከናውናል፤
- የባህል ዘርፉ ልማታዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- በባህል ዘርፍ የሕዝቡን ተሳትፎ ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝ የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- የኪነ ጥበብና ሥነጥበብ የፈጠራ ችሎታዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- የሀገሪቱ የፊልምና ተውኔት ጥበብ ሥራዎች የሚያድጉበትን አግባብ ያመቻቻል፤
- የሀገሪቱን የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገጽታ በዓለም የቱሪዝም ገበያ በስፋት ያስተዋውቃል፤ የአገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ያበረታታል፤
- የሀገሪቱ ቱሪስት መስህቦች ተለይተው እንዲታወቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣

የየአካባቢው ማኅበረሰብም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፋይ እንዲሆን የሚደረግበትን አግባብ ያመቻቻል፤

- የሃገሪቱ የተፈጥሮ ቅርሶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲ ለሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ በፌዴራል መንግሥት እንዲተዳደሩ የተሰየሙ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች አስተዳደር በአግባቡ መመራቱን ያረጋግጣል፤
- የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፣ ተፈጻሚነቱን ይቆጣጠራል፤
- በቱሪዝም የሠመረ አገልግሎት እንዲኖርና የቱሪስቶችም ደህንነት እንዲረጋገጥ የሚያስፈልገው የብዙ ወገኖች የሥራ ቅንጅት እውን እንዲሆን ለሚፈጠሩ የጋራ መድረኮች በማዕከልነት ያገለግላል፤
- በሰው ኃይል ሥልጠናና በሙያ ምክር አገልግሎት አማካይነት የቱሪዝም ሴክተርን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤
- የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አንድ ሚኒስትር እና ሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች እንዲሁም አስራአራት ዳይሬክቶሬቶች አሉት ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሚኒስቴር መሰሪያ ቤቱ ስር ሰባት ተጠሪ ተቋማት መ/ቤቶች አሉ፡፡ እነርሱም የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ዱር እንሰሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት፣ የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር እና የኢትዮጵያ ስብሰባ ማዕከል ናቸው፡፡(ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ -- ላይ ተያይዟል)

### የሰው ኃይል

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለው የሰው ኃይል ጠቅላላ ብዛት 282 ሠራተኞች ሲሆኑ ሴት 135 እና ወንድ 153 ሰራተኞች ሲሆኑ በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ማስተርስ 27 ዲግሪ 63 ፣ ዲፕሎማ 37 ቴክኒክና ሙያ 12 ሁለተኛ ደረጃ (8--12) 79 1ኛ ደረጃ (1--8) 56 እንዲሁም ማንበብና መፃፍ 8 ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

9. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰራተኞች ደመወዝና እንዲሁም ለሚያከናውናቸው ስራዎች ወጪ መሸፈኛ የሚሆነውን ገንዘብ ዋና ምንጩ በየበጀት ዓመቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚመደብለት በጀት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከ2003 -2006 ዓ.ም ገቢ በቅደም ተከተል 26,357,057፣ 42,424,338 ፤ 85,982,653 እና 64,161,002 እንዲሁም ወጪ በቅደም ተከተል 26,302,879፣ 33,890,050 ፤ 38,792,441 እና 54,487,594 ናቸው፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

10. በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ብቃት ማረጋገጥ ተግባርን በቁጠባ፤ ብቃት እና በስኬታማነት ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

11. የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003 እስከ 2006 በጀት ዓመታት ድረስ የተከናወነውን በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ብቃት ማረጋገጥ የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሲሆን በናሙና በተመረጡ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህርዳር እንዲሁም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ፊንፊኔ እና ቢሾፍቱ እንዲሁም በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤ በመገኘት መረጃዎችን በመከለስና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና እንዲሁም የመስክ ጉብኝት በማድረግ አሰራሩን በመመልከት እና በናሙና ባልተካተቱ አምስት የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች መጠይቆች (Survey Questionnaires) የተላከ ሲሆን ከድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በስተቀር ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡

## ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

12. ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ "በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ብቃት ማረጋገጥ ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና

ውጤታማ በሆነ መልኩ የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue)

13. ከላይ በተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተመርጠዋል፡፡ እነሱም

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃ መስጠት፤የፈቃድ አሰጣጥ እና ብቃት ማረጋገጥ ተግባርን በተመለከተ የዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመረጃ አያያዝ፤አደረጃጀት እና አጠቃቀም ፈጣንና ጥራት ያለው አገር አቀፍ የልውውጥ ሥርዓት የዘረጋና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣

የሚሉት ናቸው።

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

14. ከላይ የተመረጡት ሦስት የኦዲት ጭብጦች (Audit Issues) ለመመዘን የሚያስችሉ 20 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ስትራቴጂክ ዕቅዶች፣የሥራ መመሪያ እና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተጠናው መሰረታዊ የስራ ሒደት ለውጥ ጥናቶች ፣ መልካም ተሞክሮዎች፣ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) በአባሪነት ተያይዟል፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

15. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በማንኛውም አቅጣጫ ቱሪዝምን በዘላቂነት ለማልማት የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተፈጥሮአዊ ታሪካዊና ባሕላዊ መስህቦች ባለቤት ናት፡፡ ሁሉም በሴክተሩ የተሰማሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሀብቶች የዘርፉ ባለሙያዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት የአገልግሎት አሰጣጡን በዓይነትና በጥራት ደረጃውን ከፍ

በማድረግ ተገልጋዩ ለሚያገኘው የአገልግሎት እርካታ የተሻለ እንዲሆን በቅንጅት በመሥራት የሚከናወኑ ተግባራት የአሠራር ሂደት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## I. የደረጃ ምደባ ተግባር

1. ተቋማትን በደረጃ መመደብ
   - ተቋማት ብቃታቸው እንዲረጋገጥላቸው የሚቀርብ የደረጃ ምደባ ጥያቄ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ እንዲያሟሉ ያደርጋል፡፡ የወጡትን መስፈርቶች በመስጠት ገለፃ ያደርጋል፣ የተዘጋጁትን ቅፆች ይሰጣል፣ ክፍያ ይቀበላል ባንክ ያስገባል፣
   - ለብቃት ማረጋገጥ ተግባር ለተቋሙ የቀጠሮ ኘሮግራም ያወጣል፣ ለብቃት ማረጋገጥ ተግባር ባለጉዳዮች በግንባር በመቅረብ ወይም ባለቡት ቦታ ላይ ሆነው/online/ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣
   - በተቋማቱ በመገኘት የደረጃ ምደባ ግምገማ ያካሂዳል፣ የግምገማውን ውጤት ለደረጃ ምደባ ወሳኝ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ወሳኝ ኮሚቴው የደረጃ ምደባ ውሳኔ ለተገልጋዮች ያሳውቃል፣ ውሳኔውን ለተቀበሉ ዓርማና የምስክር ወረቀት ያሳውቃል፣ ውሳኔውን ላልተቀበሉ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓትን በማሳወቅ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲታይና ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፣
2. **የዳግም የደረጃ ምደባ ተግባር**
   - የተገልጋይ ጥያቄን ይቀበላል፣ ለዳግም የደረጃ ምደባ ፎርማሊቲዎችን እንዲያሟሉ ያደርጋል፣ ክፍያ ይቀበላል ወደ ባንክ ያስገባል፣ መገምገሚያ ቅፆችን ያዘጋጃል፣ ለብቃት ማረጋገጥ ተግባር ለተቋሙ የቀጠሮ ኘሮግራም ያወጣል፣ ለብቃት ማረጋገጥ ተግባር ባለጉዳዮች በግንባር በመቅረብ ወይም ባለቡት ቦታ ላይ ሆነው/online/ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣
   - በተቋማቱ በመገኘት የዳግም የደረጃ ምደባ ግምገማ ያካሂዳል፣ የግምገማውን ውጤት ለዳግም ደረጃ ምደባ ወሳኝ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ወሳኝ ኮሚቴው የዳግም የደረጃ ምደባ ውሳኔ ለተገልጋዮች ያሳውቃል፡፡ውሳኔውን ለተቀበሉ ዓርማና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ ውሳኔውን ላልተቀበሉ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓትን ያሳውቃል፡፡ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲታይና ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል እንዲሁም ያሰራጫል፡፡

### የተቋማት ብቃት ለማረጋገጥ የሚደረግ የክትትል ተግባር

- ብቃታቸው ለተረጋገጠላቸው ተቋማት የክትትል ተግባር በዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ ያካሂዳል፣

- ለክትትል ተግባር የሚሆን የመሥሪያና የማመሳከሪያ ቼክ ሊስት ያዘጋጃል፣ የክትትሉን ተግባር በተቋማት በመገኘትና በማካሄድ የተገኘውንም ውጤት ለተገልጋዩ ያሳውቃል፣ተቋማቱ ብቃታቸውን ጠብቀው ከተገኙ፣ የማበረታቻ ደብዳቤ ይጽፋል፣ ተቋማቱ ብቃታቸውን ካልጠበቁ፣ ያሉባቸውን ጉድለቶች እንዲያስተካክሉና እንዲበቁ ያደርጋል፣

## II. የብቃት ማረጋገጫ የመስጠት ተግባር

1. ለ<u>አስጎብኝ ድርጅቶች</u>
   - ዕውቅና ለሚፈልጉ ተገልጋዮች የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ መልስ ይሰጣል፣ ተገቢውን ፎርማሊቲ እንዲያሟሉ በግንባር/Online/ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ገለፃ ያደርጋል፣ ተቋማቱ በሚገኙበት ቦታ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣
   - መስፈርቱን ላሟሉ ዕውቅና ይሰጣል፣ ደረጃቸውን ያሳውቃል፣ የተቋማቱን መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፣ መስፈርቱን ላላሟሉ ተቋማት የማብቃት ሥራ ያከናውናል፣
2. <u>እውቅና ለተሰጣቸው  ተቋምት የክትትል ተግባር</u>
   - የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ለክትትል የሚውሉ ፎርማሊቲዎች ያዘጋጃል፣ የክትትል ሥራ ያካሂዳል፣ የክትትሉ ሪፖርት ያጠናቅራል፡፡ የተሰጣቸውን ብቃት  አስጠብቀው ከቀጠሉ የማበረታቻ ደብዳቤ ያሰጣል ፡፡ ካላሟሉ እንዲያሟሉ ማድረግና የማብቃት ሥራ ያከናውናል፡፡
3. <u>ለግለሰብ ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣</u>
   - ከተገልጋዮች የሚመጣውን ጥያቄ በመቀበል ተገቢውን ፎርማሊቲ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል  የመረጃ ቋት ውስጥ እንዲያዙ ያደርጋል እንዲሁም ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## 2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃ መስጠት፣ የፈቃድ አሰጣጥ እና ብቃት የማረጋገጥ ተግባርን ለመፈፀም የዘረጋው የአሰራር ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

**የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የሚመለከት ፖሊሲ አፈጻጸምን በተመለከተ**

16. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም አገልግሎቶች አሰጣጥ የሚመለከት ፖሊሲ ከሚመለከታቸው ባለድርሻና አስፈጻሚ አካላት ጋር በመመካከር ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ የወጣውን ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎችና መስፈርቶች ሊያወጣ ይገባል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲው፣ የወጡት ደንብና መመሪያዎችና መስፈርቶች ለሚመለከታቸው አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ሊያሰራጭና ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

17. ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ፖሊሲ አዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም የወጣውን ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለክልሎችና ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ያሰራጨ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የአዲስ አበባ መስተዳድር ባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች በክልልም ሆነ በዞን እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ያሉ ቢሮዎች ላይ የመመሪያዎች አፈፃፀም ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

18. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚወጡ ደንብና መመሪያዎች ተፈፃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በውክልና ኃላፊነት ለክልሎች መሰጠቱን፣መመሪያዎች ላይ አንድ አቋም ለመውሰድ እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በማስተካከል ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚላክላቸውን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የምናሳስብ ቢሆንም ነገር ግን መመሪያዎች ወጥ በሆነ መልኩ እንዳይተገበሩ በየክልሉ ያሉ የቱሪዝም ቢሮዎች አደረጃጀት የተለያየ በመሆኑ ለአሰራር ችግር መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ አሁን በሀገር አቀፍ የተቋቋመውና

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት የቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እነዚህ የባለድርሻ አካላት ተናበው ያለመስራት ችግሮችን ይፈታል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በተያዘው አመት በ2007 ዓ.ም ከአቀድናቸው ስራዎች አንዱ የህግ ማእቀፍን በተመለከተ ወጥ የሆኑ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ለክልሎች የሚሰራጩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በእቅድ ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ ለክልሎች ውክልና ከሰጡ በኃላ በውክልናው መሰረት ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆናቸው ክትትል ስለመደረጉ ምላሽ አልሰጡም፡፡

19. የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ማንዋሎች ሁሉም አስፈጻሚ አካላት ሥራ ላይ ካላዋሉትና ተግባራዊ መደረጉም ክትትል ካልተደረገ ለቱሪስቶች የሚሰጠውን አገልግሎት ጥራት ለማረጋገጥ አዳጋች ያደርገዋል፡፡


**የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃ አሰጣጥን በተመለከተ**

20. ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ሬስቶራንቶች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶችን ሊያወጣ ይገባል፡፡ በወጣውም መስፈርት መሰረት ተቋማቱን በመመዘን ለተቋማቱ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ትክክለለኛውን ደረጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ደረጃ የተሰጣቸው ተቋማት በተሰጣቸው ደረጃ መሥራታቸውን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠርና የተቋማቱን ደረጃም ተገልጋዩ ህብረተሰብ እንዲያውቀው ሊደረግ ይገባል፡፡

21. ይሁን እንጂ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣ የባህል ምግብ ቤቶች) በኮከብ ደረጃ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ ቢሆንም የሆቴሎች የደረጃ ምደባ ስራ ተጠናቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ነገር ግን በተለያየ የኮከብ ደረጃ ራሳቸውን መድበው ራሳቸውን እያስተዋወቁ ያሉ ሆቴሎች ላይም ስለአገልግሎት አሰጣጣቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የቱሪዝም ቢሮዎች የተጠናከረ የክትትል እና የቁጥጥር ስራ የማይከናወን መሆኑና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉድለት በሚታይባቸው ሆቴሎች ላይ እርምጃ የማይወሰዱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ 2003 ዓ.ም ከተዘጋጀው መስፈርት ናሙና በመውሰድ በሀዋሳ፣በባህርዳር፣በቢሾፍቱ፣እና በአዲስ አበባ ከተሞች በናሙና ከታዩት ባለሦስት ኮከብ እና ከዛ በላይ ናቸው ከሚባሉት 32 ሆቴሎች መካከል፤ መስፈርቱ የሚጠይቀውን፡- የሆቴሉ ውበትና እይታ ለእንግዶች አመቺ ያልሆኑ 9፣ በቂ የመኪና

ማቆሚያ (parking) የሌላቸው 14፣ የእንግዳ ማረፊያ (loby) ክፍል፣ የኢንተርኔት እና የፅህፈት አገልግሎት የሚሰጥበት ቢዝነስ ሴንተር የሌላቸው 15፣ የእንግዳ ንብረት ማስቀመጫ ካዝና በየክፍሉ የሌላቸው 16፣ ሲፈለግ የሚቀርብ የህፃናት አልጋ (baby coach) የሌላቸው 16፣ ሲፈለግ የሚቀርብ ተጨማሪ አልጋ (extra bed) የሌላቸው 4፣ ሱት(suite) ክፍሎቻቸውን በተመለከተ ማሟላት የሚገባቸውን ቁሳቁሶች በየክፍሉ ሻይ፤ ቡና ማፍያና ቢላ ማንኪያ ሹካ ያላሟሉ 4፣ ምግብ ቤቱን በተመለከተ 2 ምግብ ቤት (restaurant) የሌላቸው 5፣ ሁለገብ አዳራሽ (function hall) የሌላቸው 2፣ የምግብ ዝግጅት ክፍልን (kitchen) በተመለከተ በጣም ከፍተኛ በሆኑ መሳሪያዎች የተደራጀ የእቃ ማጠቢያ ክፍል የሌላቸው 3፣ የልብስ ንፅህና መስጫ ክፍል (laundary) በተመለከተ እራሱን የቻለ ዘመናዊ የማጠቢያ፤የማድረቂያ እና የመተኮሻ መሳሪያ የሌላቸው 3፣ የእቃ ግምጃ ቤት (store) በተመለከተ ቢያንስ 2 የእቃ ግምጃ ቤት የሌላቸው 2፣ ሀይጅን ንፅህና (hygiene and sanitation) በተመለከተ 2፣ ደህንነት ጥበቃ (safety and security) በተመለከተ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ ደውል የሌላቸው 11፣ ህንፃው ከ2 ፎቅ በላይ ከሆነ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌላቸው 12፣ በኮምፒውተር የታገዘ የሻንጣ መፈተሻ ማሽን የሌላቸው 15፣ ዘመናዊ የደህንነት ካሜራ (security surveillance camera) የሌላቸው 11፣ ዊልቸር (wheelchair) የሌላቸው 23፣ የሆቴሉ እንግዶች በድርጅቱ አገልግሎት ሲጠቀሙ በሚደርስባቸው አደጋ ለሚከሰት ጉዳትና እሳት አደጋ ኢንሹራንስ የሌላቸው 32፣ ሰራተኞች ማንነታቸውን የሚገልፅ የደረት ላይ መታወቂያ (ባጅ) የሌላቸው 6 ያላሟሉ ሆቴሎች ተገኝተዋል።



23. ስለጉዳዩ በናሙና በታዩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ኃላፊዎች ተጠይቀው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች) በኮከብ ደረጃ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት የተዘጋጁ ቢሆንም የሆቴሎች የደረጃ ምደባ ስራ ተጠናቆ ተግባራዊ ባለመደረጉ ምክንያት በፌደራል ደረጃ ሆነ በክልል የሚገኙ ትላልቅ ሆቴሎች ላይ የቁጥጥር ስራ ለማከናወን አስቸጋሪ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

24. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በእርግጥ የደረጃ ምደባ መስፈርት በተፈለገው ፍጥነት አለመዘጋጀቱ እና ተግባራዊ አለመደረጉ በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አገልግሎት አሰጣጥ ክትትል እና ቁጥጥር ስራ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ሆኖም ለሁሉም ከኮከብ ደረጃ በታች ለሆኑ ሆቴሎች፣ሎጆች፣ሞቴሎችና ሬስቶራንቶች የአገልግሎት ብቃታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መስፈርቶች ተዘጋጅተው የክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የክልሎችን አፈፃፀም በመከታተል ላይ ያለውን ክፍተት ወደፊት እንደሚስተካከል ገልጸዋል፡፡

25. በተጨማሪም በ 2003 ዓ.ም የወጣው ደንብ አስገዳጅ ባለመሆኑ ይህንን በሚያሟላ መልኩ ተስተካክሎ እንዲሰራበት ለማድረግ የተጀመሩ ሥራዎች አሉ ሲሉ ገልፀዋል፡፡ የደረጃ ምደባን አስመልክቶ ቀደም ሲል በ 2003 ዓ.ም የደረጃ ምደባ ስራ ተከናውኖ ነበር፡፡ ነገር ግን በመመዘኛ መስፈርትና በአፈፃፀም ላይ ከባለሀብቶች ቅሬታ ስለተነሳ መመዘኛ መስፈርቱ እንደገና በውጪ ድርጅት (DUNIRA) የተባለ የውጪ ድርጅት በጨረታ አሸንፎ እንዲጠና ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መስፈርቱ እንዲገመገም ተደርጎ በምክር ቤት ፀድቆ በአሁኑ ሰዓት የመጨረሻው ስራ ሊጠናቀቅ የቀረው ከዓለም የቱሪዝም ድርጅት በሚመጡ ባለሙያዎች ጋር የመፈራረም ሂደት ብቻ መሆኑን፣ በቀጣይነት የደረጃ ምደባውን የሚያከናውኑት በአለም የቱሪዝም ድርጅት (የውጪ ዜጎች) የሚመደቡ ባለሙያዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

26. የተዘጋጀው ደረጃና መስፈርት ለባለሆቴሎቹ እንዲያውቁትና እንዲደርሳቸው መደረጉን፣ የባለሙያ ምዳበው እንደተጠናቀቀ እንዲዘጋጁ ይህ ሲጠናቀቅ የደረጃ መስጠት ስራው ሁሉንም በአንዴ ማዳረስ ስለማይቻል በአዲስ አበባ ከሚገኙ ሆቴሎች እንደሚጀምር፣ ምዘናውም ተቋሙን እና የቀጠሩዋቸውን ባለሙያዎችን ጭምር የሚያካትት እንደሆነ፣ አዲስ አበባ በሼራተን በሥራ ላይ ላሉት ሠራተኞችን የብቃት ማረጋገጫ ፈተና (CoC)

በመስጠት ባለሙያዎቹ ምዘና መጀመሩንና በሁሉም ሆቴሎች እንደሚቀጥል በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

27. በራሳቸው በኮከብ ደረጃ እየሰጡ ያሉ ሆቴሎች ደረጃውን የሚሰጡት ከዚህ በፊት የደረጃ ምደባ ስራ በተካሄደበት ወቅት ባገኙት ለየደረጃው የተዘጋጀውን መስፈርት በመጠቀም ሊሆን እንደሚችል፣ ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉድለት በሚታይባቸው ሆቴሎች ላይ በሆቴል ማህበራት በኩል ይህንን ድርጊት እንዳይፈፅሙ ምክርና ማሳሰቢያዎች እንዲሰጥ ከማድረግ ውጭ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣) ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታይ ጉድለቶችን ለመከላከል በአዲስ አበባም ሆነ በክልል ባሉ ቱሪዝም ቢሮዎች የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ስራ እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉድለት በሚታይባቸው ሆቴሎች ላይ የእርምት እርምጃ በአግባቡ እየተወሰደ ካለመሆኑም በላይ ስልጣን በተሰጠው አካል ሳይመዘኑ ለራሳቸው ደረጃ የሚሰጡ ሆቴሎችን በተመለከተ በፍጥነት የማስተካከያ እርምጃ ካልተወሰደ ለህብረተሰቡ የተሳሳተ መረጃ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) በተመለከተ**

29. ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት ሊወጣላቸው እና ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም የባሕል ምግብ ቤቶች የአገሪቱን ባህልና ልማድ በበጎ ጎኑ የሚያንጸባርቁ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልልች የባሕል ምግብ ቤቶችና ሬስቶራንቶች ምን መስፈርት ሟሟላት እንደሚገባቸው መስፈርት እንዳልወጣላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በባሕርዳር ከተማ የቡሉናይል ሆቴል ከፊት ለፊቱ ያሉ ምግብ ቤቶች ፈቃዱን በምግብ ቤት ካወጡ በኋላ ማታ ማታ የባሕል ጭፈራ ቤቶች በመሆናቸው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ሀገር ቱሪስቶች በሆቴሉ ካረፉ በኋላ ሌሊት ከጭፈራ ቤቱ በሚወጣው ድምፅ ሰላማቸውን የሚያጡበት ሁኔታ መኖሩን ይህንን ጉዳይ ለክልሉም ሆነ ለከተማው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በተደጋጋሚ ቢያሳውቁም ምንም አይነት ምላሽ እንዳላገኙ ባለሀብቱ ገልፀዋል፡፡

31. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ምላሽ ሲሰጡ ለቱሪስት አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ የባሕል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) ደረጃ ያልወጣላቸው መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት ቤቱ ለባህል ምግብ ቤት ምቹ መሆኑን እንዲሁም በቤቱ ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች የአካባቢውን ባህል የሚወክሉ የሀገሪቱንም እሴቶች የጠበቁ መሆናቸውን የሚረጋገጥ ቢሆንም አንዳንድ የባሕል ምግብ ቤቶች ፈቃዱን ያወጡት በባሕል ምግብ ቤት ሆኖ እያለ ማታ ማታ ፈቃድ ሳይጠይቁ የባህል ምሽት ቤቶች የሚያደርጉ መኖራቸውን እንዲሁም አብዛኞቹ ቤቱን በመከራየት የሚሰሩ በመሆኑ ለዚህ ስራ ተብሎ የተዘጋጀ ቦታ ባለመሆኑና የድምፅ መከላከያ (Sound Proof) የሌላቸው በመሆኑ ከነዚህ ቤቶች የሚወጣው ድምፅ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ሰላምን እየነሳ እንደሚገኝና ድርጊቱ የሚከናወነው በምሽት በመሆኑ ለቢሮዎቹ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

32. በተጨማሪም የአገሪቱን ባህልና ልማድ ጠብቀው እየሰሩና በአገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎችን እያስተዋቁወቁ መሆኑን ለማረጋገጥና በዚህ አግባብ የማይሰሩትን የባህል ምሽት ቤቶችን ለመከታተልና አጥፊዎችንም ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

33. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በየክልሉ የሚገኙ የባህል ምሽት ቤቶች አሰራራቸውን አስመልክቶ የቅርብ ክትትል በማድረግ የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጠው በየክልሉ የሚገኙ የባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች ሲሆኑ ከሥርዓት ውጪና ባህሉን የሚበርዙ ተግባራትን በአጠቃላይ ለማስወገድ እንዲቻል የተለያዩ ውይይቶች ተደርገዋል ፡፡ በክልሎችም ተገቢው ክትትል እንዲደረግ የጋራ መግባባት ያለ ሲሆን ወደፊት በተጠናከረ ሁኔታ ችግሩን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ ተጠንቶ የሚሰራ ይሆናል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ደረጃን በተመለከተ ደግሞ ለሬስቶራንቶች የወጣው ደረጃንም ለባህላዊ ምግብ ቤቶች ለመጠቀም እንደታሰበ በመጀመሪያ የደረጃ መስጠቱ ከሆቴሎች ይጀመርና የሌሎቹ ደረጃ አሰጣጥ እንዲቀጥል መታሰቡን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡

34. ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች የባህል ምሽት ቤቶች የሚሰጡትን አገልግሎት የአገሪቱን ባህልና ልማድ ጠብቀው እንዲሰሩ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበትን የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ሀገሪቱን ሊገኙ የሚመጡ

የውጪ ሀገር ቱሪስቶችን ሆነ የአገር ውስጥ ጎብኚዎች የአካባቢውን እውነተኛ ባህል እያስተዋወቁ መሆኑን ማረጋገጥን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት አካበቢዎች ጽዳትን በተመለከተ**

35. የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች ከሚመለከታቸው የክልልና የከተማ አካላት ጋር በመተባበር አካበቢው የሚጠበቅበት መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ የሚደረግበትን ሁኔታ ሊያመቻቹ ይገባል፡፡

36. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ክልሎች መካከል በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ በአሞራ ገደል አካባቢ የፅዳት ጉድለቶች መኖራቸውና እንዲሁም የልመና ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መምጣቱ፣ በሀዋሳ ሌክ ቪው ሆቴል ፊት ለፊት ለበርካታ ዓመታት ምንም አገልግሎት የማይሰጥ በቆርቆሮ የተሰራ መጋዘን መኖሩ ሀይቁ ፊት ለፊት እንዳይታይ ማድረጉ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህርዳር ብሉ ናይል ሪዞርት በመግቢያው በር ላይ የፍሳሽ ማስወገጃ ቦይ ባለመኖሩ የተኛው ጎርፍ የሪዞርቱን ውበትና ዕይታ ከመቀነሱ ባሻገር ለእንግዶች መተላለፍያ መንገድ አስቸጋሪ መሆኑን በመስክ ኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

37. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የቱሪስት መስህብ ሥፍራዎች አካባቢ ያለውን የፅዳት ጉድለቶች እየተስፋፋ ያለውን የልመና ሥራ ለማስወገድ ከክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለማከናወን ማቀዳቸውን ገልፀዋል፡፡

38. በአንዳንድ የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት ሥፍራዎችና አካበቢያቸው ጽዳታቸው በአግባቡ አለመጠበቁና በሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት ክትትል አለመደረጉ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

**በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች ግንባታን በተመለከተ**

39. በኮከብ ደረጃ የሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የሚገነቡበት ስፍራ በከተማው ማስተር ፕላን ውስጥ ሊካተት ይገባዋል፡፡ በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ንድፍ ስራ ከመጽደቁ በፊት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የቱሪስት ቢሮዎች በኩል ለሆቴል አገልግሎት አመቺ መሆኑን የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

40. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በኮከብ ደረጃ የሚገኙ ትላልቅ ሆቴሎች የሚገነቡበት ቦታ በከተማው ማስተር ፕላን ውስጥ ተካተው አልተያዙም፣ የግንባታው ቦታም ለሆቴል አገልግሎት አመቺ መሆኑን የሚረጋገጥበት የአሰራር ስርአት በቢሮው እንደሌለ ገልጸው፣ ነገር ግን ግንባታው ከተጀመረ በኋላ መስፈርቱን ተከትሎ እንዲሰራ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል እናደርጋልን ሲሉ ገልፀዋል፡፡

41. ለባህርዳር ከተማ አስተዳደር የባህልና ቱሪዝም ስፖርት መምሪያ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ቀደም ብለው የተገነቡ ሆቴሎችን በተመለከተ ምንም አይነት የምዘና አስተያየት መስጠት ባንችልም የማስፋፊያ ስራ በሚሰሩበት ወቅት አንዳንድ ድጋፍና ክትትል የምናደርግበት ሁኔታ አለ፡፡ የህንፃው ንድፈ ሀሳብ በአግባቡ ለመገምገም ተቋሙ በሙያተኛ ደረጃ የእውቀት ጉድለት (ክፍተት) ያለበት ሲሆን ከኢንቨስትመንት ተቋምን ከከተማ ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር በመጀመሪያ ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችለው የጋራ መግባቢያ ሰነድ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም አልፎ አልፎ ከቢሮው እውቅና ውጪ የሚገነቡ ሆቴሎች እንዳሉና የምናውቃቸው ግንባታ ጀምረው ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርቡ ብቻ እንደሆነ ጨምረው ገልጸዋል፡፡ ለሆቴል ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ ሲሰሩ ቢገኙ እንኳን እርምጃ የሚወስዱበት የአሰራር ስርአት እንደሌለ አስታውቀዋል፡፡

42. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማትና አጠቃቀም የሥራ ሂደት አስተባባሪ ተጠይቀው ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ለተባለው አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡበት ሥርዓትም ሆነ በዚህ ሙያ የተመደበ ባለሙያም መ/ቤታችን የለውም ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ሴክተራችን ስለግንባታዉም ሆነ ስለፈቃዱ የሚያውቅበት የአሰራር ሥርዓት የለውም ሲሉ ገልፀዋል፡፡

43. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው በክልል ደረጃ ለሆቴል ተለይቶ የተዘጋጁ ቦታዎች በግልፅ ተለይቶ ስለመቀመጣቸው ቢሮው የሚያውቀው ነገር እንደሌለ፣ በክልሉ ትልልቅ ሆቴሎች በሚገነቡበት ወቅት አስቀድሞ ለቢሮው የማሳወቅ ክፍተት ያለ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከቢሮው ጋር የጋራ ስምምነት እንዲገቡ ከተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት ለመስራት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

44. ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ለተባለው አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ በከፍተኛ ደረጃ ክፍተት እንደሚታይ፣ ይህንን ስራ የሚከታተለው አካል ተለይቶ ስላልተቀመጠ አንዳንድ ባለሃብቶች ቦታው ለሆቴል አገልግሎት አመቺ ለመሆኑ በባለሙያ መጠናታቸውን የሚያመላክት ማስረጃ ሳይኖር ገንዘብ ስላላቸው ብቻ ፎቅ በዘፈቀደ እንደሚገነቡ ገልጸዋል፡፡ ይህንን ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ በመመሪያ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ከቢሮው እውቅና ውጪ የሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች ግንባታውን ከጨረሱ በኋላ ከቀረጥ ነፃ የተለያዩ ዕቃዎችን ለማስገባት እንዲፈቀድላቸው ከኢንቨስትመንት ቢሮ ወረቀት ይዘው ሲመጡ ነው ሆቴል እየሰሩ መሆኑን የምናውቀው እንጂ ስለ ህንፃ ይዘት ምን እንደሆነ የኛ ቢሮ የሚያየው ምንም ነገር ባለመኖሩ በዚህ በኩል ትልቅ ክፍተት ይታይበታል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

45. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀድሞ ቱሪዝም ኮሚሽን ይባል በነበረበት ሰዓት ንድፍ ስራውን የሚከታተል የምህንድስና ክፍል ነበር አሁን ግን ግንባታውን አስመልክቶ ፈቃድ የሚሰጠው ማዘጋጃ ቤት በመሆኑና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን ስራ የሚያረጋግጥ ክፍል አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ይህን ተግባር ለማከናወን በስነ ህንፃ ዘርፍ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ቀጥሮ ለማሰራት እንዲያስችል የሥራ መደቦች ተለይተው በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር እንዲፀድቅ ስለተደረገ ባለሙያዎቹ ተቀጥረው ሥራ የሚጀምሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ከተማው ለባለ ኮከብ ሆቴሎች የሚሆን ሥፍራ በመለየት እንዲያዘጋጅና ተወዳዳሪ መሆን ስለሚችሉ ለባለሀብቶች በሊዝ እንዲያቀርብ፣ ክልሎች ደግሞ እንደ የተጨባጭ ሁኔታቸው ቦታ ለይተው እንዲይዙና የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጉ ስምምነት ላይ መደረሱን ወደ ስራ የተገባ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

46. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በክልል የሚመለከታቸው አካላት በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ለተባለው አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ሆቴሉ የሚሰጠው አገልግሎት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከመፍጠሩም ባሻገር የሆቴሎች ደረጃ በሚሰጥበት ወቅት አለመግባባት ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም ሆቴሎቹ

የሚሰሩበት ስፍራ ለሆቴል ተብሎ በተለየ የተዘጋጀ ካልሆነ በመሰረተ ልማት አቅርቦት ላይም ችግር ይፈጥራል፡፡

**በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡትን የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በተመለከተ**

47. በሆቴል ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሃብቶች በህግ የተቀመጠው የመገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ የማስገባት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ባለሀብቶች የማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ሲጠይቁት የተጠየቀው ዕቃ ከሆቴል ስራ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ዝርዝሩን በማየትና በማረጋገጥ ሊፈቅድላቸው ይገባል፡፡ ወደ አገር ውስጥ በማበረታቻው ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ የሆቴል የቁሳቁስ እቃዎች፣ፊኒሽንግ ማቴሪያል እንዲሁም ተሸከርካሪዎች ሲገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ በዓይነት እና በብዛት መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም የድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በተላከ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች፣ ሎጆች እና አሰጎብኚ ድርጅቶች ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች የሚፈልጉት ዕቃ ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ደብዳቤ ከመጻፍ ውጪ የተጠየቀው ዕቃ ከስራው ጋር ያለውን ግንኙነት፣ የተጠየቀው ዕቃ ብዛትና በዓይነት የማያዩና ዕቃዎቹና መሣሪያዎቹ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ተዘርዝረው የሚያዝበት የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

49. ስለጉዳዩ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኃላፊዎች ተጠይቀው ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር በዓይነት እና በብዛት ተለይተው የሚመዘገቡበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ እቃዎችን ዝርዝር ለማዘጋጀት ከፌዴራል፣ ከአዲስ አበባ፣ ከኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ ዕቀዎችን ምዝገባን ለማከናወን ደንብ እየተዘጋጀ ሲሆን ደንብ ሲፀድቅ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የእቃዎችን ዝርዝር በዓይነት እና በብዛት ተመዝግቦ የሚያዝበት አሰራር ይዘረጋል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማበረታቻ የሚሆን ከቀረጥ ነፃ ወደአገር ውስጥ የሚገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር

በዓይነት እና በብዛት መዝግቦ ለመያዝ ትልቁ ክፍተት ማፅደቅ እና መቆጣጠር ላይ ነው የግንባታ እቃዎች ዝርዝር (Bill of quantity) የሚያዘጋጁት ባለሀብቱና ኮንትራክተሩ በመሆኑ ታማኒነቱ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ሆቴል ሲገነባ ክትትልና ቁጥጥሩ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከሚሰጠው የቀረጥ ነፃ መብት አንፃር ትልቅ የሀገር ሀብት እየባከነ ግለሰቦች ያለአግባብ የሚከብሩበት ሁኔታን ያመቻቻል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

50. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቱሪዝም አገልግሎቶች ብቃት የማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሆቴሎች የትብብር ደብዳቤውን የሚፅፈው ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መኖሩን፣ መሬት መኖሩን፣ የግንባታ ፈቃድ ማውጣቱን እና ክልሉ የሚሰጠውን አስተያየት ካየን በኋላ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የትብብር ደብዳቤውን እንጽፋለን፡፡ ይህንንም ስራ ስንሰራ ባለሀብቱ የሰጠውን የኮከብ ደረጃ ወደፊትም የደረጃ ምደባ ስራ በሚከናወንበት ወቅት የሰጠው የኮከብ ደረጃ የሚያንስ ከሆነ ከቀረጥ ነፃ ላስገባው እቃ እንደገና ቀረጥ እንዲከፍል ግዴታ እያስገባን ነው፡፡ ለወደፊቱ ግን የሚያስገቡት ዕቃዎች ዝርዝር እንዲቀርብ መደረግ እንዳለበትና በፍጥነት ለማስተካከል ዝግጁ እንደሆኑ ሚኒስትሩ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

51. ባለሃብቱ ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት የፈለገው ንብረት ዝርዝር ሳይታይና ለሚገነባው ሆቴል ጋር ያለው ተያያዥነት ሳይረጋገጥ ዕቃዎን ከቀረጥ እንዲስገባ እንዲፈቀድለት የትብብር ደብዳቤ መጻፍ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታ ተብሎ የዘረጋውን ሥርዓት የህገወጥ ተግባር እንዲፈጸምበት በር ይከፍታል፡፡

**በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች፣-ሎጆች እና አስጎብኝ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት ንብረቶች መረጃ አያያዝና ልውውጥን በተመለከተ፣**

52. የቱሪዝም አገልግሎት ለመስጠት አዲስ ኢንቨስት የሚያደርጉም ሆነ ነባር ድርጅታቸውን የማስፋፋያ ሥራ ለመስራት በመንግስት የተፈቀደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የተለያዩ የግንባታና የሆቴል መገልገያ ዕቃዎችን እንዲያስገቡ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡ በማበረታቻው ተጠቅመው የገቡት ንብረቶች ዝርዝር መረጃ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተመዝግቦ ሊያዝና የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች መረጃው እንዲደርሳቸው የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

53. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከቀረጥ ነጻ ማበረታቻ መሰረት በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች እና ሎጆች፣ አስጎብኝ ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት

የጠየቁትን፣ በማበረታቻው ተጠቅመው ያስገቡትን የግንባታ፣ የቁሳቁስ እቃዎች፣ ፊኒሽንግ ማቴሪያል እና የተሽከርካሪዎች መረጃዎችን በተደራጀ ሁኔታ መዝግቦ የማይዝ መሆኑን፣ ከቀረጥ ነፃ ስለገቡት ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት ባለሀብቱም ሆነ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያሳውቁ መሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃው እንዲደርሰው የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት የሌለው በመሆኑ መረጃው እንደማይያዝ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችላል፡፡

54. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ቀደም ሲል ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ እቃዎችን መረጃ በተደራጀ ሁኔታ ተመዝግቦ የማይዝ መሆኑን፣ወደፊቱ ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም ለክትትልና ለቁጥጥር አመቺ በሆነ መንገድ ለመስራት ጥረት እንዲሚያደርጉ የገለፁ ሲሆን ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከቀረጥ ነፃ የገቡ እቃዎችን የሚያሳውቅበት የአሰራር ስርዓት የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ይህ ስራ ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ወደፊት አሰራሩ እንዲቀጥልና መረጃ ልውውጥ እንዲኖር በጋራ የምንሰራበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከቀረጥ ነፃ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ለቱሪዝም ዘርፍ ያስገኙት ፋይዳ አስመልክቶ ዝርዝር ጥናት በተደራጀ መልኩ ያልተሰራ ቢሆንም ይህ የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተግባራዊ ከሆነ ጊዜ አንስቶ የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋማት በቁጥር እየጨመሩ ስለሚሄዱ ወደፊት ዝርዝር ጥናት ይደረጋል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

55. የቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት መሳሪያዎች፣ የመገልገያ ዕቃዎችና የግንባታ ዕቃዎች ብዛትና መጠን በትክክል አለመታወቁና በሚመለከታቸው አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመኖሩ መንግስት ዘርፉን ለማበረታታት የሰጠው ማበረታቻ ምን ያህል እንደሆነ መረዳትን አዳጋች የሚያደርግና ማበረታቻዎቹ ያስገኙትን ጥቅም ለመገምገም አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## የቱሪዝም አገልግሎትን ለማበረታታት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶች ለተባለላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን የሚደረገውን ክትትል በተመለከተ

56. ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶችም ለተባለላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ማበረታቻውንም ከተባለለት ዓላማ ውጭ ተጠቅመው የተገኙ ባለሃብቶች ላይም በህጉ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም የድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች እና ሎጆች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች እና ለነባር ድርጅቶች ማስፋፊያ በማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የተፈቀዱና ከቀረጥ ነጻ የገቡ የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በዓይነት ተዘርዝረው የሚያዙበት የአሰራር ሥርዓት ባለመኖሩና መረጃው ስለሌላቸው እቃዎቹም ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል እንደማያደርጉ ታውቋል፡፡

58. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከቀረጥ ነፃ የገቡ እቃዎች ለተባለላቸው አላማ ብቻ መዋላቸውን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በህግ የተሰጠው ስልጣን ባለመኖሩ የክትትልና ቁጥጥር ስራ እየሰራን አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

59. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መንግስት ከቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የቁሳቁስ እቃዎች፣ፊኒሽንግ ማቴሪያል እንዲሁም ተሽከርካሪዎች እንዲያስገቡ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የትብብር ደብዳቤ ከመፃፍ በስተቀር የገባው እቃ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እየሰራ ባለመሆኑ ባለሀብቶች ከቀረጥ ነፃ ወደሀገር ውስጥ ያስገቡት እቃዎች በትክክል ለተባለለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## 2.2 የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት እና አጠቃቀም ፈጣንና ጥራት ያለው ሥርዓት እንዲዘረጉ ማድረጉን እና ቱሪስቶቹን የሚመለከቱ መረጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የልውውጥ ሥርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ

### የቱሪስት አገልግሎት የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀት እና አጠቃቀምን በተመለከተ

60. ለቱሪስቶች የተሰጡ አገልግሎቶች በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝርዝር መረጃ ሊይዙ ይገባል፡፡ እነዚህ መረጃዎችም ለሚመለከተው የክልል ቱሪዝም በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቅሮ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃዎች በክልልና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የሚለዋወጡበት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ቴክኖሎጂ ሊደገፍ ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን መረጃዎች በተጠናቀረ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

62. በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና የድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቱሪስቶቹን የሚመለከቱ መረጃዎች ሰብስቦና አደራጅቶ እንዲይዙ ለማድረግና ለእነርሱም እንዲያሳውቋቸው ለማድረግ የተጀመሩ ጅምር ሥራዎች መኖራቸውን ነገር ግን የመረጃ ፍሰቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

63. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመረጃ አያያዝ ላይ ክፍተት መኖሩን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መካከል የመረጃ ፍሰት ልውውጥ በሦስት፣ በስድስት፣ በዘጠኝ ወራት እና ከክለሎች ጋር በአመት የመረጃ ልውውጥ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚደረግ የልውውጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱን፣ ይህን ችግር ለመቅረፍ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ አመት (በ2007ዓ.ም) በዳይሬክቶሬት ደረጃ ስታስቲክስ ዲፓርትመንት ተቋቁሞ የመረጃ አያያዝንና አጠቃቀምን ዘመናዊ ለማድረግ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

64. በተጨማሪም የቱሪስቶችን እርካታ ለመለካት የአለምአቀፍ ጎብኚዎች የቆይታቸውን ጊዜ አጠናቀው ሲወጡ ያላቸውን አስተያየት በመጠይቅ ተሰብስቦና ተተንትኖ ውጤቱ (International Visitors’ Exit Survey: Phase I) ሰኔ 2005 መዘጋጀቱን፣ የቱሪዝም ስታትስቲካል ዘገባ (Tourism Statistics Bulletin) በሚኒስቴር መ/ቤቱ መዘጋጀቱን፣ ወጥ የሆነና የተሟላ መረጃ ከአገልግሎት ሰጪዎች በክልሎች እየተሰበሰበ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅቱን ጠበቆ እንዲደርስ ለማድረግ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ለመክፈት ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ መሆኑን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ላይ ገልጸዋል፡፡

65. ለቱሪስት የተሰጡ አገልግሎት እና ሌሎች ቱሪዝም ነክ መረጃዎች በአገልግሎት ሰጪዎቹም ሆነ ዘርፉ በሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተጠናቅሮ አለመያዙና ወቅቱን የጠበቀና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ አለመኖሩ አገሪቱ በዘርፉ እያከናወነች ያለችውን ሥራ ለማወቅም ሆነ ያጋጠሙ ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታታ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## 2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ

**የቱሪስት አገልግሎት በሚሰጡ የዘርፍ ተቋማትና የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋርያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ**

66. ባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና በክልል ያሉ ቱሪዝም ቢሮዎች፣በየደረጃው ያሉ ለቱሪስት አገልግሎት የሚውሉ የኢንቨስትመንት፣ የግንባታ፣ የንግድ ፈቃድ ወዘተ በሚሰጡ አካላት መካከል የደረጃ ፣ የፈቃድ አሰጣጥ እና የብቃት ማረጋገጥን ተግባር በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን በመካከላቸው የጠበቀ የስራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለደረጃ ሆቴሎች የድጋፍ አሰጣጥ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተናቦ የመስራት ችግር ያለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

68. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና እንዲሁም በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሥራ ክፍሎች መካከል የስራ ግንኙነት እና ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን ነገር ግን በተጠናከረ መልኩ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልሎች ጋር ያለው ግንኙነትም የተጠናከረ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ከአንዳንድ መ/ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ችግር አለ (የንግድ ፍቃድ የሚሰጡ አካላት ንግድና እንዱስትሪ ቢሮ ተባባሪ አይደሉም፡፡ ለአንዳንድ ድርጅቶች ከቢሮው እውቅና ውጪ የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ሳያደርጉ ፍቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩን አክለው ገልፀዋል፡፡

69. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በቱሪዝም ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የተለያዩ ድጋፍና ትብብር እንዲያገኙ ከኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በመተባባር ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የትብብር ደብዳቤ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የምንፅፍበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ከቀረጥ ነፃ ያስገቡትን ተሽከርካሪ በአግባቡ ስራ ላይ ማዋላቸውን በተመለከተ ከትራንስፖርት ባለስልጣንና ከገቢዎች ጉምሩክ

ባለስልጣን ጋር በመተባበር የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር አናሳ መሆኑን በተጨማሪም የብቃት ማረጋገጥ ስራን አስመልክቶ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖር መስፈርቱ ተዘጋጅቶ እየተሰራበት ቢሆንም ጥራቱን ጠብቆ ይከናወናል ለማለት ግን አያስደፍርም ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከንግድ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ጋር በተያያዘ ከንግድ ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸውን በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡

70. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላት እና ከሌሎች አስፈፃሚ መ/ቤቶች መካከል በተጠናከረ መልኩ ተቀናጅቶ የሚሰሩበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ  የቱሪዝም ዘርፉ ላይ ለሚሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች የሚደረገውን ድጋፍ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

**የቱሪዝም አገልግሎት መስጪያ ተቋማት የፈጠሩትን የሥራ ዕድል  በተመለከተ**

71. በሀገሪቱ ውስጥ በቱሪዝም አገልግሎት የተሰማሩ ተቋማት በከተሞችም ውስጥ ሆነ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ሲቋቋሙ  የሚቀጥሯቸው ሰራተኞች ቢያንስ 70 ከመቶው የአካባቢው ህብረተሰብ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ሊያመቻቹ ይገባል፡፡ የሚቀጠሩ ሠራተኞች የቱሪዝም እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት ያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች ለማረጋገጥ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይም ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በምክክር ሊሰሩ ይገባል፡፡

72. ይሁን እንጂ በሀገሪቱ በከተሞችም ሆነ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች ከዘርፉ ከሚገኘው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ በተሰማሩ ባለሀብቶች/ድርጅቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ እና በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ግንኙነት ባለመኖሩ እንዲሁም የቱሪዝም እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት የሰለጠነ የሰው ኃይል በየአካበቢው ለማፍራት የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ የአካባቢ ሕብረተሰቦች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እያደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

73. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ተጠይቀው በሀገሪቱ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ የሚቋቋሙ የቱሪዝም አገልግሎት መስጪያ ተቋማቶች የሚቀጥሯቸው ሰራተኞች ቢያንስ 70 ከመቶው የአካባቢው ህብረተሰብ

ያማከለ ለማድረግ ቢፈለግም የሚቀጠሩ ሠራተኞች የቱሪዝም እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት ያሚሉ ለማድረግ በአገሪቱ በዚህ ሴክተር ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማግኘት እጅግ ከባድ ሆኗል፡፡ ነገር ግን በተቻለ አቅም የአካባቢው ህብረተሰብ የሥራ ዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባላቸው ደረጃ ላይ የሙያ ክህሎታቸውን ለማሳደግ በሥልጠና እንዲታገዙ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

74. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የሆቴሎችና የሪዞርቶች ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በከተሞችም ሆነ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች የሆቴል እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት ያላቸው የሰለጠነ የሰው ኃይል የማያገኙ መሆኑና በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ለመቅጠር ከፍተኛ የሆነ ውድድር መኖሩን ገልፀዋል ፡፡

75. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ በሰጡት መልስ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቁጥራቸው እንዲጨምር ወቅታዊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በአልፎ አልፎ የሚሰጥ ቢሆንም በበጀት እጥረት ምክንያት የሚቋረጥበት ሁኔታ መኖሩ፣ የማሰልጠኛ ተቋማት የጥራት ደረጃና የመቀበል አቅም ውስን መሆኑ እንዲሁም በገበያ ላይ በዘርፉ የሰለጠነ የባለሙያ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ በመኖሩ ችግሮቹን ለመቅረፍ ከሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ተቋማት ቴክኒክና ሙያ (TVET) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የጋራ ስምምነት ለመፈራረም የተለያዩ ስራዎች ለመስራት በጅምር ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

76. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የእንዱስትሪው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሠራተኞቻቸው የሙያ እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የስልጠና ዓይነቶች በአጭርና በረጅም ተለይተው በሁሉም ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሶ በጋራ እቅድ ለመምራት በዝግጅት ላይ ነን ሲሉ ገልፀዋል፡፡ በቀጣይነት ለኢንዱስትሪው የሚያስፈልውን የሰው ኃይል ለማሰልጠን አሁን ያለው መነሻ ሁኔታ (Baseline survey) የተከናወነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በየክልሉ የሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች የአካባቢው ተወላጆች ናቸው ሙያን ለማሳደግና ለማሻሻል እንዲቻል የሚኒስቴር መ/ቤቱ አካል የሆነው የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል በየመዳረሻው በመገኘት ስልጠና በመስጠት እገዛ እያደረገ ይገኛል::

77. በቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ በተሰማሩ ባለሀብቶች/ድርጅቶች፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እና በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ግንኙነት ባለመኖሩ፣ ኢንቨስትመንቱ በሚከናወንበት አካበቢ የቱሪዝም እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት ያሟላ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዳይኖርና የአካባቢ ሕብረተሰቦች ከሚፈጠረው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

**በኮከብ ደረጃ ላሉ ሆቴሎች የሚሰጥ በውጪ ምንዛሪ የመገበያየት ፈቃድን በተመለከተ**

78. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ የሆኑ በኮከብ ደረጃ ያሉ ሆቴሎች ደንበኞቻቸውን በውጭ ምንዛሪ ከማተናገዳቸው በፊት ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ፈቃዱን እንዲያገኙ ለባለሀብቶቹ ተገቢውን ድጋፍ ሊደርግ ይገባል፡፡ ፈቃድ የወሰዱ ባለሀብቶችም ፈቃዳቸውን በየአመቱ ሊያድሱ ይገባል፡፡

79. በኦዲቱ ወቅት ከብሔራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ እንግዶቻቸውን ለማተናገድ ፈቃድ ለማውጣት ባለሀብቶች የሚኒስቴር መ/ቤቱን የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ሲጠይቁ እንደሚሰጣቸው ታውቋል፡፡ በዚህ መሰረት ብሔራዊ ባንክ እስከ ግንቦት 2 ቀን 2006 ዓ.ም (እ.ኤ.አ እስከ 10/05/2014) ድረስ ደንበኞቻቸውን በማስተናገድ በውጪ ምንዛሪ ገንዘብ የመሰብሰብ ፈቃድ ከሰጣቸው 175 ድርጅቶች ውስጥ 108 ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች ፣ሎጆች፣ ሪዞርቶች እና አስጎብኚ ድርጅቶች ሲሆኑ በ 2006 ዓ.ም 10 ያላሳደሱ 27 ፈቃድ ካወጡ ዓመት ያልሆናቸው ናቸው፡፡

80. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ተጠይቀው በኮከብ ደረጃ ያሉ ሆቴሎች የውጪ ሀገር ዜጎችን ለማስተናገድ በውጪ ምንዛሪ የመሰብሰብ ፈቃድ እንዲያገኙ ባለሀብቶቹ የትብብር ደብዳቤ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይፃፍልን ብለው በሚያመለክቱት መሰረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚጽፉ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ዙሪያ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚችል አካል ባለመኖሩ በአብዛኛው ፈቃድ ሳያወጡ በሕገወጥ መንገድ የውጪ ምንዛሪ የሚሰበስቡ ሆቴሎችም መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

81. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ለብሔራዊ ባንክ ላይሰንሲንግ ኢንስፔክሽን ዋና ክፍል ኃላፊ ተጠይቀው ለቱሪስቶች አገልግሎት የሚሰጡት ተቋማት በውጭ ምንዛሪ የግብይት ፈቃድ የምንሰጠው ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኮከብ ደረጃ ናቸው ብሎ በላከልን

ማረጋገጫ መሰረት እንጂ ባንኩ የኮከብ ደረጃ ይኑራቸው አይኑራቸው የማረጋገጥ ሥራ እንደማይሰራ ገልጸዋል፡፡ ፈቃድ ጠያቂዎች ባንኩ ያወጣውን መስፈርት አሟልተው መገኘታቸውን ቦታው ድረስ በመሄድ በራሱ ባለሙያ ከተረጋገጠ በኋላ ከአፈፃፀም መመሪያ ጋር ፈቃዱ ይሰጣቸዋል፡፡ ድርጅቶችም ባገኙት ፈቃድና ባንኩ ባወጣው መመሪያ መሰረት የውጪ ምንዛሪ በመቀበል ስራቸውን ያከናውናሉ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኙ በሕገወጥ መንገድ የሚሰሩትን ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የያዘ ኮሚቴ ተቋቁሞ አንዳንድ ስራዎች የተጀመሩ ቢሆንም የተጠናከረ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

82. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በኮኮብ ደረጃ ያሉ ሆቴሎች በውጪ ምንዛሬ ግብይት የሚያደርጉበትን ፍቃድ እንዲሰጣቸው ለብሄራዊ ባንክ የትብብር ደብዳቤ እንፅፋለን እንጂ ፈቃድ ስለማግኘታቸው እና በየአመቱ ስለማደሳቸው የመቆጣጠር እና የመከታተል ስልጣን ያለው ብሔራዊ ባንክ ቢሆንም በጋራ ተናበን ለመሥራት አቅደናል ብለዋል፡፡

83. በውጪ ምንዛሪ የመሰብሰብ ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኙት በአግባቡ እየሰሩ መሆኑና በየወቅቱ ማሳደሳቸው፣ ሌለችም ፈቃድ ከባንኩ ሳይወስዱ በውጭ ምንዛሪ እንዳይገበያዩ ለማድረግ የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ ለህገወጥ የገንዘብ ዝውውር በር ይከፍታል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

84. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም ብቃት ማረጋገጥ ተግባርን ለማከናወን የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ማንዋሎች ተግባራዊ ስለመደረጋቸው የተጠናከረ ክትትል አለመኖሩ፣
- ለሆቴሎች፣ ለሎጆችና ለሬስቶራንቶች የሚሰጡት አገልግሎት ተመዝኖ ደረጃ ያልወጣላቸውና ለራሳቸው ደረጃ እየሰጡ ለተገልጋዩ የተሳሳተ መረጃ የሚሰጡ መሆኑንና እንደዚህ በሚያደርጉት ላይ የዕርምት ዕርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፣
- ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት ተብለው የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት ያልወጣላቸውና ስለአገልግሎት አሰጣጣቸው የሚደረግ ክትትል አለመኖሩ፣
- የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ መገምገሚያ መስፈርቶች ለመተካት የተዘጋጀው የደረጃ አሰጣጥ መስፈርት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት ሥፍራዎችና አካባቢያቸው ጽዳታቸው በአግባቡ የተጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ በሚመለከታቸው አካላት መካከል በቅንጅት ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በክልል የሚመለከታቸው አካላት በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ለተባለው አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የቱሪዝም ቢሮዎች የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት የትብብር ደብዳቤ ሲጠይቁ ለማስገባት የፈለጓቸው መሳሪያዎች፣ የመገልገያ ዕቃዎችና የግንባታ ዕቃዎች ምንነት፣ ብዛትና መጠን ባለህብቱ ከሚገነበው ሆቴል ጋር ያለው ተያያዥነት ሳይታይና ሳይረጋገጥ፣ የኮከብ ደረጃቸውንም ሳያረጋግጥ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ እንዲፈቀድ የትብብር ደብዳቤ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚፃፍ መሆኑ፣

- የቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት መሳሪያዎች፣ የመገልገያ ዕቃዎችና የግንባታ ዕቃዎች ብዛትና መጠን በትክክል አለመታወቁና በሚመለከታቸው አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመኖሩ፣ ንብረቶቹም ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የክትትልና የቁጥጥር ሥራ የማይሰራ መሆኑ፣
- ለቱሪስት የተሰጡ አገልግሎት እና ሌሎች ቱሪዝም ነክ መረጃዎች በአገልግሎት ሰጪዎቹም ሆነ ዘርፉ በሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተጠናቅሮ አለመያዙና ወቅቱን የጠበቀና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ ዘዴ አለመኖሩ፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላት ከሌሎች አስፈፃሚ መ/ቤቶች መካከል በተጠናከረ መልኩ ተቀናጅቶ የሚሰሩበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፣
- በቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ በተሰማሩ ባለሀብቶች/ድርጅቶች፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እና በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል ለዘርፉ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ለማፍራት ጠንካራ የሥራ ግንኙነት አለመኖሩ፣
- በውጪ ምንዛሪ የመሰብሰብ ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኙት በአግባቡ እየሰሩ መሆኑና በየወቅቱ ማሳደሳቸው፣ ሌሎችም ፈቃድ ከባንኩ ሳይወስዱ በውጭ ምንዛሪ እንዳይገበያዩ ለማድረግ የተዘረጋ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ፣

ታውቋል፡፡

85. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶችና ችግሮች ለማስወገድ ወይል ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

86. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም ብቃት ማረጋገጥ ተግባርን ለማከናወን የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡-

- የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ማንዋሎች በሁሉም አስፈጻሚ አካላት ሥራ ላይ ተግባራዊ መደረጉም በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልል ቱሪዝም ቢሮዎች ክትትል ሊያደርጉና በአፈጻጸም ላይ በሚያጋጥሙ ችግሮችም አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣) የአዘጋጀውን የኮከብ ደረጃ ምደባ ሥራ በአፋጣኝ በመጀመር ደረጃ በመስጠት ተገልጋዩ ህብረተሰብም ለሚከፍለው ዋጋ ትክክለኛ አገልግሎት እንዲያገኝ ሊደረግና በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚታይ ጉድለቶችን ለመከላከል በአዲስ አበባም ሆነ በክልል ባሉ ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ስራ የሚሠራበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በውጭ ባለሙያዎች የደረጃ አሰጣጥ ሲከናወን የክህሎትና የሙያ ሽግግር እንዲኖር የሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የሚመለከታቸው የክልል ባለሙያዎች አብረው የሚሳተፉበት ሁኔታ የሚመቻችበት መንገድ ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች የባህል ምሽት ቤቶች የሚሰጡትን አገልግሎት ምን መስፈርት ማሟላት እንደሚገባቸው የሚያሳውቅ ግልጽ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግና ተፈጻሚነቱም ላይ በሚመለከታቸው አካላት ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበትን የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት ሥፍራዎችና አካባቢያቸው ጽዳታቸው በአግባቡ የተጠበቀና ለተገልጋዮቹ ጥሩ መስህብ እንዲሆኑ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የክልልና የከተማ መስተዳደሮች ጋር በቅንጅት ክትትል እየተደረገ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡


- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በክልል የሚመለከታቸው አካላት በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ባለሀብቱ ሊሰራው ካሰበው ሆቴል ደረጃና ለሚጠበቅበት አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ቱሪዝም ቢሮዎች የሚያረጋግጡበት ወይም አስተያየት የሚሰጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሆቴሎቹ የሚሰሩበት ስፍራ ለሆቴል ተብሎ በየከተሞቹ ማስተር ፕላን ተለይቶ በተቀመጠ ሥፍራ ሊሆንና አስፈላጊው መሰረተ ልማት በቅድሚያ ሊሟላላቸው ትገባል፡፡
- በሆቴል ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት የትብብር ደብዳቤ ሲጠይቁ ለማገባት የፈለጉትን የዕቃ ዝርዝር ከሚገነቡት ሆቴል ጋር ያለው ተያያዥነት በአይነትና በብዛት አስፈላጊነቱ እያየና እያረጋገጠ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ እንዲፈቀድላቸው የትብብር ደብዳቤ ሊጽፍ ይገባል፡፡ ለክትትል ያመችም ዘንድ መረጃውን አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡
- የቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት መሳሪያዎች፣ የመገልገያ ዕቃዎችና የግንባታ ዕቃዎች ብዛትና መጠን በትክክል እንዲታወቅ በሚመለከታቸው አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ የገቡት ዕቃዎችም ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና ከክልል የቱሪዝም ቢሮዎ ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለቱሪዝም ፖሊሲ ማሻሻያ እንዲረዳና አገሪቱ ከዘርፉ ያገኘችውን ጥቅም በግልጽ ለመረዳት እንዲቻል ለቱሪስት የተሰጡ አገልግሎት እና ሌሎች ቱሪዝም ነክ መረጃዎች በአገልግሎት ሰጪዎቹም ሆነ ዘርፉ በሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተጠናቅሮ በመያዝ ወቅቱን የጠበቀና ቀልጣፋ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላት እና ከሌሎች የግንባታ፣ የፈቃድ እና የመሠረተ ልማት አቅራቢ ተቋማትና አስፈፃሚ መ/ቤቶች መካከል በተጠናከረ መልኩ ተቀናጅቶ የሚሰሩበት የተጠናቀረ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲታገዝ ባለሀብቶች/ድርጅቶች እና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ማሰልጠኛ ተቋማትን ጨምሮ ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ለማፍራት

በመካከላቸው  ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና የምክክር መድረክ ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ የሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች ለተፈጻሚነቱ ሁኔታዎቹን ሊያመቻቹ  ይገባል፡፡

- በውጪ ምንዛሪ የመሰብሰብ ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኙት በአግባቡ መስራታቸውን፣ ፈቃዳቸውን በየወቅቱ ማሳደሳቸው እና ከባንኩ ፈቃድ ሳይወስዱ በውጭ ምንዛሪ እንዳይገበያዩ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርገቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና መረጃ የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች እና በናሙና ተመርጠው የታዩ ሆቴሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| የኦዲት ጭብጥ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|
| I. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብቃት የማረጋገጥ፣ ፈቃድ የመስጠት እና ደረጃ የማውጣት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤ | 1.1 የሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም አገልግሎቶች አሰጣጥ የሚመለከት ፖሊሲ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1..2 የወጣውን ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያወጣ ይገባል፡፡ |
| | 1.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፖሊሲ፣ደንብና መመሪያዎቹ ሲያዘጋጅ ባለድርሻ አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡ |
| | 1.4 የወጡት ደንብና መመሪያዎች ለሚመለከታቸው አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ሊሰራጭና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች ወ.ዘ.ተ) ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶችን ሊያወጣ ይገባል፡፡ በወጣው መስፈርት መሰረት ለተቋማቱ ደረጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.6 ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት ሊወጣላቸው እና ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| | 1.7 የሚወጣውም መስፈርትና ደረጃ የአገሪቱን ባህልና ልማድ በበጎ ጎኑ የሚያንጸባርቅ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.8 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የብቃት ደረጃቸውን ለመገምገም የተዘጋጀው መስፈርቱ የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በየጊዜው የሚከለስበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.9 ሚኒስቴር መቤቱ የደንቦቹንና መመሪያዎቹን ተፈጻሚነትን የሚያረጋግጥበት የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.10 ክልሎች የሚያከናውኑት የቱሪስቶች አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ብቃት ለማረጋገጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣውን ደንብ መሰረት በማድረግ እንደየክልላቸው ተጫባጭ ሁኔታ የአፈጻጸም መመሪያ ሊያዘጋጁና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.11 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደረጃ ምደባ ሥራ የሚሳተፉ መዳቢዎችን ለመመረጥ የሚረዳ ሙያው የሚጠይቀውን አስፈላጊ የሥነ ምግባር፣ እውቀትና ክህሎትን ያካተተ መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.12 በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃ አሰጣጥ ምደባ ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ወቅታዊ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያለው የሙያና የሥነ ምግባር ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.13 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.14 ከተሰጣቸው ደረጃቸው በታች አገልግሎት በሚሰጡ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የዕርምት ዕርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 1.15 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በክልል የሚመለከታቸው አካላት በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ለተባለው አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.16 ወደ ተለያዩ ክልሎች የሚመጡ ጎብኝዎች የአገሪቱን ተፈጥሮአዊ ባህላዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህቦችን በአግባቡ እንዲረዱ የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ አስጎብኚ ባለሙያዎች /ቱር.ጋይዶች/ ማንዋል በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.17 በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች እና ሎጆች፣ አስጎብኝ ድርጅቶች ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች እንዲሁም የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.18 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማበረታቻ የሚሆን ከቀረጥ ነፃ ወደአገር ውስጥ የሚገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር በዓይነት እና በብዛት መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 1.19 ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶችም ለተባለላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና የውል ግዴታ ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 1.20 የአስጎብኚ ድርጅቶች ለአስጎብኚነት የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች የየድርጅታቸውን አርማ የመለጠፍ ስራ ከመከናወኑ በፊት የወጣውን መስፈርት መሰረት በማድረግ በቅድሚያ ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሟሟላታቸውን አረጋግጦ ፈቃድ የሚሰጥበትን የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| **II. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የመረጃ አያያዝ፤አደረጃጀት እና አጠቃቀም ፈጣንና ጥራት ያለው ሥርዓት እንዲዘረጉ እና ቱሪስቶቹን የሚመለከቱ መረጃዎች አገር አቀፍ የልውውጥ ሥርዓቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ፤** | 2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቱሪስቶቹን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፤ አደረጃጀት እና አጠቃቀም ፈጣንና ጥራት ያለው እንዲሆን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አገር አቀፍ የልውውጥ ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል |
| | 2.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ የባለድርሻ አካላትን መረጃዎችን አሰባስቦና አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቱሪስቶችን ፍላጎት ለማርካት በኮከብ ደረጃ ያሉ ሆቴሎችን የመኝታ ክፍሎችን ብዛት ፣የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ፣ የተጎበኙ ቦታዎችና የጎብኝዎች ብዛት የተሟላ መረጃ አጠናቅረው ሊይዙ ይገባል፡፡ |
| | 2.4 በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል ያለው የመረጃ ፍሰት ልውውጥ ቋሚ የሆነ የጊዜ ገደብ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 2.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በመረጃ አያያዝ ላይ ስልጠናና ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም ክትትል ሊያደርግ ይገባል |
| | 2.6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅታዊ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ በማያደርጉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ እርምጃ የሚወስድበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.7 በየዓመቱ ለቱሪስት አገልግሎት ለመስጠት በማለት ከቀረጥ ነጻ ዕቃዎችን ለማስገባት የተጠየቁና ወደ አገር ውስጥ የገቡ መረጃዎች ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 2.8 ለቱሪስቶች የተሰጡ አገልግሎቶችን እና ሌሎች ቱሪዝም ነክ መረጃዎች ዘርፉ በሚመለከታቸው አካላት መካከል ልውውጥ የሚደረግበት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.9 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ የክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ቱሪስቶች በቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የአገኙትን የአገልግሎት እርካታ በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎችም ሆነ አስተያየቶችን የሚሰበሰቡበትንና የሚተነተኑበትን ሥርዓት ተዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 2.10 በተደረገው ትንተና መሰረት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚረዱ ማሻሻያዎችንና የማስተካከያ እርምጃዎች በሚመለከታቸው አካላት ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| III. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣** | 3.1 ቱሪዝም ሚኒስቴር እና በክልል ያሉ ቱሪዝም ቢሮዎች የደረጃ ፣ የፈቃድ አሰጣጥ እና የብቃት ማረጋገጥን ተግባር ወጥነት ያለው ሆኖ ለማከናወን በሥራ ክፍሎች መካከል የጠበቀ የስራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል |
| | 3.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ በሚከናወኑ የልማትና የክትትል ስራ ላይ የጋራ ስትራቴጂያዊ አስተሳሰብና ቅንጅታዊ አሰራርን መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ የባለድርሻ አካላት ሊያዘጋጅና ሊተገብር ይገባል፡፡ |
| | 3.3 የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቁጥራቸው እንዲጨምር ወቅታዊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ከሆቴልና ቱሪዝም ስራ ካሉ ማሰልጠኛ ተቋም ጋር በመተባበር በጥናትና ምርምር የተደገፈ ሙያዊ ስልጠናና የምክር አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 3.4 ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ ለሚሰጣቸው የተለያዩ ስልጠናዎች እና ምክር አገልግሎት ዙሪያ ስልጠናውን የወሰዱ ተቋማት በስራ ላይ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 3.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየደረጃው የሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃ የሚወስኑ ወቅታዊ የድጋፍ የክትትልና ግብረ መልስ ተግባራትን የሚፈጽሙና የሚመሩ የየክልሎች ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎችን በማደራጀት አቅማቸው እንዲያጎለብቱ ማድረግ አለበት፡፡ |
| | 3.6 ሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል ቱሪዝም ቢሮዎች በሀገሪቱ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ የሚቋቋሙ የቱሪዝም አገልግሎት መስጫያ ተቋማቶች የሚቀጥሯቸው ሰራተኞች ቢያንስ 70 ከመቶው የአካባቢው ህብረተሰብ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡ |
| | 3.7 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ የሆኑ በኮከብ ደረጃ ያሉ ሆቴሎች የውጪ ሀገር ዜጎችን ለማስተናገድ በውጪ ምንዛሪ የመሰብሰብ ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ሊያገኝ ይገባል፡፡ |
| | 3.8 በውጪ ምንዛሪ የተሰበሰበው ገንዘብ ሲመነዘር በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጠው አካል ብቻ በኩል ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 3.9 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የየበጀት ዓመቱ የዕቅድ ግምገማና ክትትል ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 3.10 ዕቅድ ሲከለስ በሚመከለተው አካል ቀርቦ ሊፀድቅ ይገባል፡፡ |